# ፍ ት ሻ - ል ብ ወ ለ ድ
# ክ ፍ ል ሁ ለ ት

*ከሥርጉተ ሥላሴ*
*ነሐሴ 2000 ዓ.ም.*

ተረት - ተረት
የላም - በረት ... አላችሁ ልጆች ?...

ባለፈው ጊዜ በፍትሻ የልደት ቀን ባቢና ማሚ በገዙላት የልብስ ቀለም ፍትሻ መጀመሪያ ላይ አልቅሳ ነበር። በኋላ ግን ባቢና ማሚ የምትፈልጋቸውን ቀለማት ያላቸው ልብሶች እንደሚገዙላት ቃል ስለገቡላት በደስታ የልደት ባዕሏ እንደተፈፀመ ነበር ተረትተረቱ ... ያቆመው።

ዛሬ ልጆች ታሪኩ ከቆመበት እንቀጥላለን ...

አዎን ልጆች በፍትሻ የልደት ቀን ፍትሻ ብዙ ሥራ ነው የነበረባት። ትምህርት ቤት መሄድ፣ መማር፣ ስትመለስ ደግሞ የልደት በዓሏ ሰለነበር ጓደኞቿን በማስተናገድ ማሚን በሥራ ማገዝ ስለነበረባት ፍትሻ ድክም አላት።... ከዛ ... ባቢና ማሚን ጉንጯቸውን ስማ ወደ መኝታ ክፍሏ ስትገባ ባቢ እንደተለመደው አብሮአት ተከትሏት ወደ መኝታ ክፍሏ ገባና ስለ አንድ አንበሳ ታሪክ እያጫወታት እያለ ... ባቢ ሳይጨርስ እሷ ለምን እንቅልፍ አይወስዳትም መሰላችሁ። ...

ከዛ ባቢ እንዳትቀሰቀስ - ከእንቅልፏ እንዳትነቃ በጥንቃቄ ቀስ አድርጎ የመኝታ ክፍሏን በር ዘግቶ ሄደ። ... እና መኝታ ክፍሉ ገብቶ ተኛ። ማሚ ግን ነገ ፍትሻ ትምህርት ስላላት ለትምህርት ቤት የሚሆናትን ልብሷን አዘጋጅታ፤ እንዲሁም እራት የተበላበትን ዕቃ ሁሉ አጣጥባ፣ የእንግዳ መቀበያውን ክፍል ስታሰናዳ በጣም አምሽታ ነበር የተኛችው። ባቢና ማሚ በአንድ መኝታ ክፍል ሲተኙ ፍትሻ ደግሞ ከግሏ መኝታ ክፍል ተኝታለች። ... ሦስቱም ደክሟቸው ስለነበረ ወዲያው እንደተኙ እንቅልፍ ወሰዳቸው። ...

ሲነጋ -- ወፎች ነግቷል - ተነሱ - ወደ እዬሰራቸው ተሰማሩ ሲሉ ማሚ ተነሳች። ሁልጊዜ ፍትሻ ነበር ቀድማ የምትነሳው። ዛሬ ግን ፍትሻ ዘገዬች። ደክሟት - ወይንስ እንቅልፍ ይዟት ይሆን? በማለት ማሚ ወደ ፍትሻ መኝታ ክፍል ስትገባ ፍትሻ የለችም። ...

እህ ! አለች ማሚ ... ወደ መፀዳጃ - ቤቱም - ወደ ምግብ የሚዘጋጅበት ክፍልም - ወደ መታጠቢያ ቤቱም ብትሄድ ፍትሻ የለችም። ወይኔ - ማሚ - ደነገጠች። ከዛ - ወደ ጓሮው ሄደች። ... ፍትሻ እዬተንከባከበች ውሃ እየጠጣች ያሳደገቻት አንዷት ደስ የምትል አበባ ስላለቻት እሷን ውሃ እያጠጣች ይሆናል ብላ ስትሄድም እዛም ፍትሻ የለችም። ... ወይኔ ማሚ ጉዱ ... ጩነቃት - ወደነ ባቢ መኝታ ክፍል ሄዳ ፍትሻ ቤት ውስጥም፣ በግቢም እንደሌለች ለአባቷ ስትነግረው ተያይዘው ተላቀሱ።...

ኡ ኡታቸውን በጋራ ለቀቁት። ... ኡ ኡታቸውን የሰሙ ጎረቤቶች እየተሯሯጡ መጡ። ከዛ በኋላ ፍትሻን ፍለጋ በዬአቅጣጫው ተሰማሩ ... ግን ልጆች ፍትሻ የት - ሄዳ ይሆን - ትገኝስ ይሆን ? ባቢና ማሚስ እንዴት ይሆኑ ይሆን ?

**... በቀጣዩ ተረት ተረት ክፍለ 3 እናየዋለን እሺ ?...**